

## ☙38-2❧

# እግዚአብሔር ከእኛ ምን ይፈልጋል

## በብዙ ነገር ታግሰን እንድንኖር

**ለ) በመከራችን እንታገስ**

“መታገስ” ማለት የተለያየ ክፉ ነገር ሲደርስብን ተስፋ ሳንቆርጥ መቆም ማለት ነው። “ክፉ ነገር” ስንል ከላይ እንደገለጽነው አንደኛው በሰዎች መገፋት ነው። ዮሴፍ በወንድሞቹ ተሸጠ፣ ዳዊት በሳኦል እጅ ተሰደደ፣ ኢየሱስ በአይሁድ ሕዝብ ተሰቀለ። ይህን ዓይነቱ በሰዎች ምክንያት የሚደርሰው መከራ ነው። ሌላው ደግሞ በራሱ በሰይጣን ልክ በኢዮብ ላይ እንደደረሰው በእኛም ላይ እጁን ሲዘረጋ ነው። ሌላው ደግሞ እራሱ እግዚአብሔር የቅጣቱን በትር ሲሰነዝርብን የሚሰማን ህመም ነው። በመከራችን መታገስ የምንችልበትን ኃይል የምናገኘው፥ በመጨረሻ ሁሉም ነገር ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ውጪ እንደማይወጣና ሁሉም ነገር ለበጎ እንደሚሆንልን አምነን የተቀበን እንደሆነ ነው (ሮሜ 15፥4)። የአብርሃም፣ የያዕቆብ፣ የዮሴፍ፣ የዳዊት እንዲሁም የኢዮብ ታሪክ የተጻፈው እግዚአብሔር በእነዚህ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ለመሥራት ሁኔታዎችን በመለወጥና በማስተካከል ለእነርሱ በጎነት፣ ለእርሱ ክብር እንዲሆን እንዳደረገ መረጃ እንዲሆን ታሪካቸው ተጻፈ። እነዚህን ምሳሌዎች ስናይ እግዚአብሔር ሁኔታዎችን ሁሉ በእርሱ ቁጥጥር እንደሚያውል እንገነዘባለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ “አንድ በልቤ ውስጥ የሚቃጠል፣ በአዕምሮዬ ውስጥ የሚመላለስ፣ የሕይወቴ ዋና ዓላማ አለ። ያም ኢየሱስን አውቅ ዘንድ ነው” አለ። “ኢየሱስን አውቅ ዘንድ ነው” ሲል ምን ማለቱ ነበር? እንደ እውነቱ ከእርሱ የበለጠ ኢየሱስን ማን ያውቃል? ይሁን እንጂ ባለው እውቀት አልረካም። ስለዚህ ትልቁ ምኞቱ ክርስቶስን በመከራው መምሰልን ነበር። መከራ የኢየሱስን ባህሪ በውስጣችን ይቅርጻል። ይኸውም፥

ሀ) ኢየሱስን በመከራው ስንመስለው፥ እርሱ የሌሎች ሞት እንዲሁም የሚደርስባቸው መከራና ችግር ገብቶትና ተሰምቶት ለእነርሱ አዝኖ በሞቱ ዕዳቸውን እደከፈለ፥ እኛም የሌሎች መከራና ችግር እንዲገባንና እንዲሰማን ይሆናል። ጳውሎስ “ስለ ወንድሞቼ ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን እጸልይ ነበር” (ሮሜ 9፥3) ሲል ሙሴ ደግሞ “የእሥራኤልን ሕዝብ ይቅር የማትል ከሆነ፥ ስሜን ከሕይወት መዝገብህ ፋቅ” ሲል ወደ እግዚአብሄር ጮኸ።

ለ) መከራ የኢየሱስን መልክ በሕይወታችን የሚቀርጽበት ሌላ መንገድ አለው። ጳውሎስ “በመከራችን እንደሰታለን፤ እንመካለን” ይላል (ሮሜ 5፥3)። ጳውሎስ ይህን ሲል ዝም ብሎ ያለ ምክንያት አይደለም። ጳውሎስ በብዙ መከራ ውስጥ አልፎአል (2ቆሮ 11፥23-27)። ይሁን እንጂ የደረሰበት መከራ መራራ አላደረገውም፤ ደስታውን አልገፈፈውም፤ ዓላማውን አላስለወጠውም፤ እግዚአብሔር በሕይወቱ ያቀደውን ዓላማ እንዲጨናገፍ አላደረገም። ነገር ግን መከራው ይበልጥ እምነቱን ስለ አጠነከረለት ጠቀመው እንጂ አልጎዳውም። መከራ ሲደርስበት ታግሶ ከመከራው ባሻገር ራቅ አድርጎ መመልከት ቻለ። በመከራው ስላገኘው ጥቅም ሲናገር “በመከራችን እንደሰታለን፤ እነመካለን፤ ምክንያቱም ከመከራ ትዕግሥት እንደሚገኝ እናውቃለን” አለ (ሮሜ 5፥3)። ጴጥሮስም ይህ በአማኞች ላይ የሚደርሰው መከራ በመጨረሻ ምን ዓይነት ውጤት እንደሚያመጣ ገልጿል። “ለጥቂት ጊዜ መከራ ከተቀበላችሁ በኋላ ፍጹሞች ያደርጋችኋል፤ ያጸናችኋል፤ ያበረታችኋልም” ይላል (1 ጴጥ 1፥5)።

ሐ) ኢየሱስን በመከራው መምሰል ማለት “ታዛዥነት” መማር ማለት ነው። ኢየሱስ እራሱ የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም በመከራው መታዘዝን ተማረ (ዕብ 5፥8)። ኢየሱስ መታዘዝን የተማረው፥ የማይታዘዝ ኃጢአተኛ ሆኖ አይደለም። ነገር ግን ሕይወቱን መስዋዕት አድርጎ እስኪሰጥ ድረስ መታዘዙን ለዓለም ሊያሳይ ነው። እኛ ግን በኃጢአታችን ምክንያት አንታዘዝም። በራሳችን ውሳኔና ምርጫ ለመራመድ እንፈልጋለን። ኢየሱስ “መንገዱ ይሄ ነው” ብሎ ሲያመለክተን፥ ፊታችንን አዙረን በሌላ አቅጣጫ መራመድ እንጀምራለን። ኢየሱስ ግን በመከራው ውስጥ እያለ እንኳን “የአንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ የእኔ ፈቃድ አይሁን” በማለት ታዘዘ። እኛም በመከራ ውስጥ ስናልፍ መታዘዝን እንማራለን።

### ሐ) ጌታን በመጠበቅ እንታገስ

በሕይወታችን መታገስን መማር የሚገባን አንዱ ክፍል እግዚአብሔር በሕይወታችን የሚሠራበትን የጊዜ ክልል መጠበቅ ስንችል ነው። አንዳንድ ችግሮች በሕይወታችን መፍትሄ እንዲያገኙ ለረጅም ጊዜ ጸልየን ይሆናል። እኛ ብቻ ሳንሆን ብዙዎችም በትዕግሥት ጠብቀዋል። አብርሃምና ሣራ የይስሀቅን መወለድ እስከ መጨረሻው መጠበቅ አቅቷቸው የራሳቸውን እርምጃ እንደወሰዱና ለሁለቱም የእስማኤል መወለድ የውስጥ ህመም እንደሆነባቸው እናውቃለን። አንዳንዶቻችን እንደ አብርሃምና እንደ ሣራ እግዚአብሔር ከወሰነው ጊዜ ቀደም ብሎ እንዲፈጽም ለመግፋት መሞከራችን አይቀርም። ዳዊት እግዚአብሔር ፕላኑን በሕይወቱ እንዲፈጽም እግዚአብሔር በትዕግሥት ጠበቀ። "እግዚአብሔር እንዲረዳኝ በትዕግስት ተጠባበቅሁት። እርሱም ጩኸቴን ሰምቶ ልመናዬን ተቀበለኝ። ከአደገኛ ጉድጓድና ከረገረግ ጭቃ አወጣኝ፤ በዓለትም ላይ በደህና አቆመኝ፤ ጉዳት እንዳይደርስብኝም አደረገ" (መዝ. 40፥1-2)።

### መታገስ ያቃታቸው

እግዚአብሔርን በትዕግሥት መጠበቅ ሲያቅተን ሁሉ ነገር ጨልሞ ይታየናል። የምናየው ጉምና ተራራ ብቻ ነው። ያኔ ሕይወታችን በማጉረምረም፣ በጥያቄና በጥርጣሬ ይሞላል።

"እግዚአብሔር ፍቅር ነው" (1 ዮሐ 4፥8) የሚለውን አውቃለሁ፤ ግን እኔን አይወደኝም፤ ቢወደኝ ኖሮ እንዴት..."

"ትዳሬ ሲፈርስ ለምን ዝም ይላል?"

"ሥራ አጥቼ የሰው እጅ እያየሁ እንድኖር ለምን ይፈልጋል?"

"በዓለም ላይ ብቻዬን እንድኖር የተፈጠርኩ ሰው ነኝ፤ ማንም የሚወደኝ የለም፤ ትዳር ስጠኝ ብዬ ለረጅም ዘመን ለምኜዋለሁ፤ ግን እንኳን ለትዳር የሚጠይቀኝ ቀርቶ ዞር ብሎም የሚያየኝ የለም"

"የክርስትና እምነቴ ምንም አልጠቀመኝም። ዓለማዊ ጓደኞቼ ሁሉ ነገር ተሳክቶላቸው ደስ ብሏቸው ሲኖሩ አያለሁ። ብዙ ታግሼአለሁ፤ ከእንግዲህ ሁሉንም እርግፍ አድርጌ ወደ ዓለም ጭልጥ ብዬ መግባቴ ነው"

"በደል ተገኝቶብኝ ምናልባት ሊቀጣኝ ሲል ይሆናል ይሄ ሁሉ ነገር በሕይወቴ ሲደርስብኝ ዝም ያለው"

"እግዚአብሔርን ቅን ፈራጅ ሆኖ አላገኘሁትም። እንደ ልባቸው በኃጢአት ለሚጫወቱት፥ ሁሉን ነገር ያሳካላቸዋል። እርሱን ተማምኜ ለተቀመጥኩት ለእኔ ግን ለምጠይቀው ጥያቄ አንድም መልስ አይሰጠኝም" ይላሉ።

እግዚአብሔርን በትዕግሥት መጠበቅ አቅቶን ስለ እግዚአብሔር ያለን አስተያየትና ግምት መስመር የለቀቀ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እኛ እንድምንገልጸው ዓይነት አይደለም ይኸውም፥

1) እግዚአብሔር ፍቅሩ እንደ ሰው የሚለዋወጥ ቦግ ብልጭ የሚል ሁኔታችንን አይቶ የሚከዳን አይደለም። "እናንተን ሁልጊዜ እወዳችኋለሁ" ይለናል (ኤር 31፥3)።
2) ሳንወደው እንኳን ይወደናል (ሮሜ 5፥8)። አኩርፈን ስንሸሸው እንኳን "ይውጣላችሁ" ብሎ ዝም አይለንም። እንደ ሰው የሚያኮርፈን ቢሆን ኖሮ ምን እንሆን ነበር?
3) እግዚአብሔር ወዳጃችን እንጂ ጠላታችን አይደለም። ከእኛ ወገን እንጂ ከጠላት ወገን አይደለም (ሮሜ 8፥31-32)።
4) እግዚአብሔር ለሁላችንም ተጨባጭ የሆነ ፕላን አለው። ለእኛ ያለውም ፕላን በጎ እንጂ ክፉ አይደለም (ኤር 29፥11-13)።
5) የእግዚአብሔር ሥራ በሕይወታችን ትክክል ነው። እኛን የሚጎዳንን ነገር ፈጽሞ በሕይወታችን አያደርግም (ዳንኤል 9፥14)። ስለዚህ "እግዚአብሔር አይወደንም፤ እግዚአብሔር ቃሉን አይጠብቅም፤ በሕይወቴ የምፈልገውን ነገር ያልሰጠኝ ሊጎዳኝ ነው፤ ሌሎችን እንጂ እኔን እግዚአብሔር አይወደኝም" ብለን ልንከስሰው አንችልም።

### በመታገሳቸው ያሸነፉ

1) መከራን የታገሰ እንደ እዮብ የለም። ንብረቱ ሲወድምበት፣ አሥሩ ልጆቹ ሲሞቱበት፣ በማማረር ፋንታ "እግዚአብሔር ሰጥቶኝ ነበር፥ እግዚአብሔር መልሶ ወሰደብኝ፤ የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን" አለ (ኢዮብ 1፥22)። በተጨማሪ ሰይጣን "ኢዮብን ከራስ ጠጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ በከባድ ቁስል እንዲሠቃይ አደረገው" (ኢዮብ 2፥7)። ያም ቢሆን እምነቱን አላናወጠበትም። "እግዚአብሔር መልካም ነገር ሲሰጠን በደስታ እንቀበላለን፤ ታዲያ መከራ ሲያመጣብን በእርሱ ላይ ማጉረምረም ይገባናል?" አለ።

2) ዮሴፍ የጎዱትን ወንድሞቹን በመበቀል ፈንታ በይቅርታ ተቀበላቸው። ወንድሞቹ በቅንአት ተሞልተው

ከአካባቢያቸቸው ሊያጠፉት አስበው ወደ ግብጽ ለሚሄዱ ነጋዴዎች በሃያ ብር ሸጡት (ዘፍ 37፥28)። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ስለነበር፥ በግብጽ ምድር ከፍ አደረገው። ከብዙ ዓመት በኋላ የሸጡትን ወንድሞቹን ሲያይ በመበቀል ፈንታ ልቡ በይቅርታና በፍቅር ተሞልቶ "እኔ ወደ ግብጽ የሸጣችሁኝ ወንድማችሁ ዮሴፍ ነኝ፤ ነገር ግን ይህን በማድረጋችሁ በመጸጸት አትበሳጩ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር እኔን አስቀድሞ የላከኝ የሰዎችን ሕይወት እንዳተርፍ ነው" (ዘፍ 45፥4-5) በማለት አጽናናቸው። እኛስ በሰዎች ተገፍተናል? ከሆነ የበደሉንን ማቀፍ እንዳለብን ቃሉ ያስተምረናል (1ጴጥ 3፥9)።

3) ሙሴ እግዚአብሔርን ለአርባ ዓመት በትዕግሥት ጠበቀ። እሥራኤላውያን ከግብጽ ባርነት መውጣት አስቸኳይ ቢሆንም፥ በቅድሚያ ሙሴ ራሱ በደንብ የታሸ መሪ እንዲሆን፥ እግዚአብሔር ከግብጽ ቤተ መንግሥት አውጥቶ በበረሃ ለ40 ዓመት የበግ ጠባቂ አደረገው። 40 ዓመት ረጅም ቢመስልም፥ ከእግዚአብሔር የጊዜ ገደብ ውጪ መሥራት እንደማይቻል ሙሴ ተገንዘበ። ለረጅም ጊዜ ጌታን ጠይቀነው ተስፋ የቆረጥንበት ነገር ይኖር ይሆን? አዎን! በሰው ተስፋ ይቆረጣል፤ በጌታ ግን ተስፋ አይቆረጥምና በትዕግሥት እንጠብቀው።

..................................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**